# የካውንስሊንግ ሳይኮሎጂ ፕሮግራምና አገልግሎት በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲና በተለያዩ አካባቢዎች ለማጠናከር የተደረጉ ጥረቶችና ያጋጠሙ ተግዳራቶች

*ወርቅነህ ከበደ እና ኖኅ ውብሸት*

***መግቢያ:*** *"Counseling" የሚለው የእንግሊዘኛ ቃል በኢትዮጵያ ከተዋወቀበት ከ1960 ዎቹ ጀምሮ በተለምዶ "የምክር አገልግሎት" በመባል ሲተረጎም ቆይቷል። ቀደምት የሙያው ሰዎችም ሆኑ አሁን በስራው ላይ ያሉት ባለሙያዎች "ምክር" በሚለው ላይ ሲስማሙ አይታዩም እንደ ምክንያትም የሚያነሱት፤ በምክር ሂደት ውስጥ የሰጪና የተቀባይ ግንኙነት ጎልቶ መታየቱ ሲሆን ይልቁንም ከሞያው እውነተኛ ባህሪ በመነሳት "ምክክር" በማለት ይተረጉሙታል ። ከሁለቱም ወገን ተሳትፎ ያለው፤ የጠባቂነት ስሜት እና ጥገኝነት የሌለበት ነው በማለት። በጥቅሉ ካውንስሊንግን በዚህ መልክ ልንገልጸው እንችላለን፤ "የካውንስሊንግ አገልግሎት በግል ወይም በቡድን በሚመጣ ፍላጎት ግብ ላይ መሰረት አድርጎ በተገልጋዩ እና በካውንስሊንግ ባለሙያው መካከል የሚደረግ ሙያዊ የዕገዛ ግንኙነት ነው" እንደ የዘመኑም የተለያዩ ዕድገቶችን እያሳየ ሙያው ዛሬ ያለበት ደረጃ ላይ የደረሰ ሲሆን በሀገራችን ኢትዮጵያ የካውንስሊንግ አገልግሎት እንደ አብዛኞዎቹ የዘመናዊ ትምህርት እና የሙያ ዓይነቶች መነሻውን ከቀድሞ ቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ ዩኒቨርሲቲ (የአሁኑ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ) ትምህርትና ስልጠና ጋር ይያያዛል። እንደሚታወቀው ላለፉት በርከት ያሉ ዓመታት በሀገራችን ኢትዮጵያ የካውንስሊንግ ሳይኮሎጂ ሞያም ሆነ ትምህርት በአግባቡ እና በተደራጀ መልኩ ታሪካዊ አመጣጡ፣ በየወቅቱ ያለፋቸው ሂደቶች፣ ተግዳራቶቹና በአጠቃላይ አሁን ያለበትንም ነባራዊ ሁኔታ በፅሑፍ፣ በተንቀሳቃሽ ምስል እንዲሁም በሌሎች መንገዶች ተደራጅቶ አልተቀመጠም ። ይህንን ክፍተት ለመሙላት እንዲረዳ ይህ የካውንስሊንግ ሳይኮሎጂ ፕሮግራምን በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲና በተለያዩ አካባቢዎች ለማጠናከር የተደረጉ ጥረቶችና የጋጠሙ ተግዳሮቶች በሚል ይህ አጠር ያለ ፅሑፍ ተዘጋጅቷል። ፅሁፉም በቀጣይ በዚሁ ርዕስ ላይ ለሚጠናከሩ ምርምሮች (ጥናታዊ ፅሑፍ፣ ዶክመንተሪ (ዳሰሳዊ ፊልም)) እንደ መነሻነትም ያገለግላል። ይህንንም ፅሁፍ ባዘጋጀንበት ወቅት በቃለ-መጠይቁ ላይ መረጃዎችን በመስጠት በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሳይኮሎጂ ትምህርት ክፍል አባላትና በውጪም በስራው ዓለም ያሉ የተወሰኑ ባለሞያዎች ተሳትፈዋል። እነዚህም በሞያው አንጋፋ ከሆኑት ጀምሮ እስከ ወጣት ባለሙያዎች ድረስ የበኩላቸውን አስተዋፅኦ አድርገዋል። በተጨማሪም መረጃዎች በተደራጀ መልኩ ካለመኖራቸው የተነሳ በርከት ያሉ ክፍተቶች ቢፈጠሩም ክፍተቶቹን ለመሙላት የተለያዩ ግለሰቦች በፅሁፍ የሚገኙ ሰነዶችን በመስጠት ተባብረውናል። በአጠቃላይ አብዛኛዎቹ መረጃዎች ከግለሰቦች በቃለ-መጠይቅ (Interview) የተገኙ ሲሆኑ የተቀሩት ከተለያዩ ድርሰናት የተጠናከሩ ናቸው።*

## የካውንስሊንግ ሳይኮሎጂ ታሪካዊ አጀማመር በኢትዮጵያ

የያኔው ቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ ዩኒቨርሲቲ በ 47 ተማሪዎች ከተከፈተ በኋላ እስከ 1950 ዎቹ ዓ.ም መጀመሪያ በግቢው ውስጥ የካውንስሊንግ አገልግሎት የሚሰጡ አነስተኛ ቢሮዎች ነበሩ። ሆኖም አገልግሎቱ በማን እና እንዴት ይሰጥ እንደ ነበር የሚጠቁሙ በቂ መረጃዎች የሉም። በ1966 ዓ.ም የሳይኮሎጂ ዲፓርትመንት ከተቋቋመ በኋላ ባሉት ዓመታት ውስጥ በአጠቃላይ በአገሪቱ አንድ

የ3ኛ ዲግሪ ካውንስሊንግ ሳይኮሎጂስትና ከአምስት የማይበልጡ የሰለጠኑ የትምህርት ቤት ጋይዳንስና ካውንስሊንግ ባለሙያዎች ብቻ ነበሩ (የሱፍ ዑ.

አብዲ, **1967** ዓ.ም)። በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ውስጥም በአንዳንድ በጎ ፍቃደኛ የሳይኮሎጂ መምህራን እና አንዳንዴም ከሙያው ጋር ምንም ግንኙነት በሌላቸው ሰዎች አገልግሎቱ ሲሰጥ ነበር። በተለያዩ ጊዜያት እንደነ ወ/ሮ ቦሰና እና ሌሎች በተማሪዎች ዲን ጽ/ቤት ስር ተቀጥረው በተማሪዎች ዲን ቢሮ ህንጻ ላይ ይሰሩ እንደነበር መረጃዎች ይጠቁማሉ።

በንጉሱ የመጨረሻ የስልጣን ዓመታት ላይ ይነሱ የነበሩ አመፆችን ለማብረድ በተለይም የተማሪውን እንቅስቃሴ ከ2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ቆርጦ ለማስቀረት በማሰብ ለጋይዳንስና ካውንስሊንግ ትምህርት ዘርፍ ትኩረት መስጠት ተጀመረ። ከጅምሩ አንስቶ አሁን እስካለንበት ድረስ ለካውንስሊንግ ትምህርት የበለጠ ትኩረት ሲሰጥ ይታያል። ይህም የሆነው ከጋይዳንስ ይልቅ ካውንስሊንግ የሳይኮሎጂ ይዘቱ ስለሚልቅ ነው። የጋይዳንስ አገልግሎት በየትኛውም ግለሰብ ሊሰጥ የሚችል ሆኖ የካውንስሊንግ አገልግሎት በተቃራኒው ጥልቅ የሳይኮሎጂ ዕውቀትን የሚጠይቅና በርካታ ሙያዊ ትግበራዎችን የሚያካትት ነው። በ1960 ዎቹ መጀመሪያ ከተማሪዎች አጠናን ልምድና የፈተና ዝግጅት ጋር በተያያዘ ብቅ ብሎ ነበር። ለዚህም ማሳያው በ1962 ዓ.ም በተደረገው የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ርዕሰ መምህራን ጉባኤ የተማሪዎች ጋይዳንስና ካውንስሊንግ አገልግሎት በመሰረታዊ ጉዳይነት ተነስቶ በዓመቱ በ1963 ዓ.ም በኢትዮጵያ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አገልግሎቱ ተግባራዊ እንዲሆን ተደርጎ ነበር።

በ1980 ዓ.ም ትምህርት ሚኒስቴር በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የካውንስሊንግ ሳይኮሎጂ ባለሙያዎችን የስራ ድርሻ (Job Description) ያዘጋጀ ሲሆን በጠቅላላው ተማሪዎችና መምህራንን በተለያዩ ግላዊ፣ ማህበራዊ፣ ስነ ልቦናዊ እና ትምህርታዊ ጉዳዮችን የማማከር፣ ለትምህርት ቤቱ የሚጠቅሙ የምርምርና ጥናታዊ ፅሁፎችን ማዘጋጀት፣ እንዲሁም የልዩ ፍላጎት ባለሙያነትንም ሚና ደርቦ መስራት እንዳለበት ያስቀምጣል። ይህም የሳይኮሎጂ ዲፓርትመንት ለልዩ ፍላጎት ትምህርት ትኩረት እንዲሰጥ የራሱ አስተዋፅኦ አድርጓል ተብሎ ይታሰባል። በተለያዩ ወቅቶችም የተማሪዎች ጋይዳንስና ካውንስሊንግ አገልግሎት በመንግስት ትኩረት የተሰጠው እና የተነፈገው ሲሆን 1980 ዓ.ም ትምህርት ሚኒስቴር ከትምህርት ብክነትና ከተማሪዎች ስነ-ምግባር ጋር በተያያዘ መፍትሄ ለማምጣት ሁሉም ትምህርት ቤቶች የጋይዳንስና ካውንስሊንግ አገልግሎት መስጠት እንዳለባቸው አሳውቆ ነበር። በወቅቱም በሀገሪቱ ውስጥ ከሁለት መቶ የማይበልጡ የመጀመሪያ ዲግሪ ያላቸው ሳይኮሎጂስቶች የነበሩ ሲሆን ነገር ግን በሁሉም ትምህርት ቤቶች አገልግሎቱን መስጠት አልተቻለም ነበር። በተመሳሳይ አገልግሎቱን ይሰጡ የነበሩትም ሙያዊ በሆነ መልኩ የተደገፉ አልነበሩም፣ የትምህርት ዝግጅታቸውም የመጀመሪያ ዲግሪ ስልጠና በመሆኑ በሙሉ አቅምና ብቃት የካውንስሊንግ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል አልነበረም። በቀጥታ ከካውንስሊንግ ሳይኮሎጂ ጋር የሚገናኙት ኮርሶች ከማነሳቸው በተጨማሪ ስኩል ካውንስሊንግ እንደ ኮርስ አለመሰጠቱና የተቀሩትም የካውንስሊንግ ኮርሶች በጥልቀት ስለማይዳሰሱ በተደጋጋሚ ከተማሪዎች ቅሬታ ይቀርብባቸው ነበር።

ትምህርቱን የሚሰጡ መምህራን እጥረትም እንደ እንቅፋት ሊታይ የሚችል ሲሆን ከተመረቁም ቡኃላ

በተመደቡባቸው ትምህርት ቤቶች አርፋጅ ተማሪዎችን የመቆጣጠር፣ የዲሲፒሊን ጉዳዮችን የመከታተል፣ የተጎዳኝ ትምህርቶችን የማስተባበርና የመምራት አንዳንዴም የግብረገብነት ትምህርት ይሰጡ ነበር፤ ከቅርብ ዓመታት ወዲህም የስነ-ዜጋና ስነ-ምግባር ትምህርትም በማስተማር ላይ ይገኛሉ። በ1982 ዓ.ም በሀገሪቱ ከነበሩት ሁለት ዩኒቨርስቲዎችና አስራ ሶስት የመምህራን ማሰልጠኛ ትምህርት ተቋማት አራቱ ብቻ የጋይዳንስና ካውንስሊንግ አገልግሎት ይሰጡ የነበረ ሲሆን አራቱም በባለሙያዎች የሚመሩ አልነበሩም (የሱፍ ዑ. አብዲ, እና ሌሎችም 1982, ዓ. ም) ።

በ1981 ዓ.ም በተደረገ ጥናት በ130 የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የጋይዳንስና ካውንስሊንግ አገልግሎት ሰጪዎች የነበሩ ቢሆንም ሁሉም በመጀመሪያ ዲግሪ ሳይኮሎጂስትነት ሞያ የሰለጠኑ ነበሩ (ኢትዮጵያን ሄራልድ፣ የካቲት 16፣ 1981)፣ አበበች 1981)። እንዲሁም በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የአዲስ ተማሪዎች ምደባን ምክንያት በማድረግ የዩኒቨርስቲው የግንዛቤ ማስጨበጫ ዝግጅቶች ላይ በመገኘት የሳይኮሎጂ ት/ክፍል መምህራን ለረጅም ዓመታት በተከታታይ አጫጭር ስልጠናዎችን ሰጥተዋል። ይህንንም በማሳደግ መደበኛ በሆነ መልኩ ለተማሪዎች የጋይዳንስና ካውንስሊንግ አገልግሎት ለመስጠት በተለያየ ወቅት በሳይኮሎጂ ዲፓርትመንት በኩል ጥረት ተደርጎ የነበረ ቢሆንም በዩኒቨርሲቲው አስተዳደር አስፈላጊው ድጋፍ ባለማግኘቱ ሳይሳካ ቀርቷል። እንደ ምክንያት የሚቀርበውም ዩኒቨርሲቲው የራሱ የሆነ የካውንስሊነግ ማዕከል አለው በሚል ነበር።

የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የተማሪዎች የጋይዳንስና ካውንስሊንግ አገልግሎት ማዕከላትም እስከ መስከረም 1991 ዓ.ም የካውንስሊንግ አገልግሎት ሲሰጡ ቢቆዩም ከመንግስት ይህ ነው የተባለ ትኩረት በማጣታቸው ተዳክመው ነበረ (የሱፍ ዑ. አብዲ, 1991, ዓ.ም)። ይህም በ1987 ዓ.ም ከፀደቀው የትምህርት እና ስልጠና ፖሊሲ (Education and Training Policy, April, 1994) እንዲሁም ሌሎች ተያያዥ ማስተግበሪያ ሰነዶች ስለ ተማሪዎች ጋይዳንስና ካውንስሊንግ አገልግሎት አስፈላጊው ትኩረት ባለመስጠታቸው ሊሆን ይችላል። በተያያዘም አንጋፋው አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ እስከ 2006 ዓ.ም ድረስ የነበሩት የዩኒቨርሲቲው መተዳደሪያ ደንቦች (Senate legislations) ስለተማሪዎች ጋይዳንስና ካውንስሊንግ አገልግሎት በተመለከተ ምንም ዓይነት ድንጋጌዎች ያልነበሩባቸው ሲሆን በ2006 ዓ.ም ተሻሽሎ የወጣው የዩኒቨርስቲው መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 78 የተማሪዎች ጋይዳንስና ካውንስሊንግ ማዕከልን የማቋቋምና የማስተባበርን ስልጣን ለተማሪዎች ዲን ፅህፈት ቤት ይሰጣል። በዋናነት ግን በየኮሌጁ በሚቋቋሙ የጋይዳንስና ካውንስሊንግ ማዕከላት አገልግሎቱ እንደሚሰጥ ያስቀምጣል። አገልግሎቱም ከትምህርት ክፍል ምደባ ጋር በተያያዙ ጉዳዮች፣ ተማሪዎች በዩኒቨርስቲው በሚኖራቸው ቆይታ በሚገጥሙዋቸው ስነልቦናዊ፣ ማህበራዊና ትምህርታዊ ችግሮችና መፍትሄዎች ላይ ያጠነጥናል።

በ1960 ዎቹ መጀመሪያ የዩናይትድ ስቴትስ የሰላም ጎድ ቡድን በጆን ኤፍ ኬኔዲ ሀሳብ አመንጪነት ወደ ኢትዮጵያ እና ወደ ተለያዩ የዓለም ሀገራት መግባታቸውን ተከትሎ ብዙ ስራዎችን የሰሩ ሲሆን ከነዚህም አንዱ የተማሪዎች የካውንስሊንግ አገልግሎት እንቅስቃሴ ነበር። በአንዳንድ ትምህርት ቤቶች ላይ በአሜሪካውያን ዘይቤ የተቃኘ የካውንስሊንግ አገልግሎት ሊሰጡ የተሞከሩ

ቢሆንም፤ ከባህልና አኗኗር ልዩነት በተነሳ ውጤታማ ሳይሆን ቀር ቷል (የሱፍ ዑ. አብዲ, 1967)።

ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ውጪ እንደ ኮተቤ መምህራን ኮሌጅ ያሉ የትምህርት ተቋማት እና የካቲት 66 ፖለቲካ ትምህርት ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት የየራሳቸውን አስተዋፅኦ አበርክተዋል። በ1980 ዎቹ መጨረሻ በወ/ሮ ሰሚራ አላሀዲ መስራችነት የጋይዳንስና ካውንስሊንግ አገልግሎት መስጫ ቢሮ በኮተቤ መምህራን ኮሌጅ የተከፈተ ሲሆን በዋናነትም ተማሪዎች በግቢ ውስጥ ለሚያጋጥማቸው ማህበራዊና ስነ ልቦናዊ እንዲሁም ትምህርታዊ ችግሮች ለምሳሌ ውጤታማ የአጠናን ስልቶችን፣ የፈተና ፍርሃትን መቋቋሚያ ክህሎቶችን፣ የማስታወሻ አያያዝ ዘዴን፣ የጊዜ አጠቃቀምን እና የተለያዩ የህይወት የክህሎት ስልጠናዎች ላይ ይሰራ ነበር።

የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ትምህርት ፋኩልቲ ከተመሰረተ ከዓመታት በኋላ የሳይኮሎጂ ዲፓርትመንት በ1966 ዓ.ም ብቁ የጋይዳንስና ካውንስሊንግ አገልግሎት ባለሙያዎች ማፍራትን ቀዳሚ ዓላማው በማድረግ ተቋቋመ። ነገር ግን በስርዓተ ትምህርት ከተካተቱት ኮርሶች ውስጥ በጋይዳንስ እና ካውንስሊነግ ትምህርት የሚሰጡ ኮርሶች የይዘት ጥልቀትና የኮርስ ብዛት አነስተኛ ነበር። በሙሉ አቅሙ በ1966 ዓ.ም የኢዱኬሽናል ሳይኮሎጂ ዲፓርትመንት ስራ ከመጀመሩ በፊት በ1958/59 የትምህርት ዘመን የመጀመሪያው የካውንስሊንግ ኮርስ የሆነው "Principles of Guidance and Counseling" መሰጠት ጀምሮ ነበር። በወቅቱም ዶ/ር የሱፍ ዑመር አብዲ ብቸኛው የካውንስሊንግ ሳይኮሎጂ ባለሙያ እና መምህር የነበሩ ሲሆን ከ1961 እስከ እልፈተ ህይወታቸው እስከ 2000 ዓ.ም በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለረጅም ዓመታት በብቸኝነት የካውንስሊንግ ትምህርትን ሲያስተምሩ እና በሙሉ አቅማቸው ሙያውን በመንግስትም ሆነ በህብረተሰቡ ዘንድ ሲያስተዋውቁ የቆዩ እንዲሁም እንደ አንዳንዶች አገላለፅ የኢትዮጵያ ካውንስሊንግ ሳይኮሎጂ ጀማሪ መምህርና ባለሙያ እንደነበሩ ይገልፃሉ። ዶ/ር የሱፍ ዑመር አብዲ የመጀመሪያውን በግል የሚተዳደረውን የካውንስሊንግ አገልግሎት መስጫ ተቋም በሀገራችን በመመስረትና አገልግሎቱ እንዲተዋወቅ ፈር ቀዳጅ መሆናቸውንም ለማረጋገጥ ተችሏል።

ከመጀመሪያው እና ብቸኛ ከነበሩት ዶ/ር የሱፍ ዑመር አብዲ በመቀጠል ወ/ሮ ሰሚራ አልሃዲ በካውንስሊንግ ሳይኮሎጂ ሙያ በመምህርነትና አገልግሎቱን በመስጠት ትልቅ አስተዋፅኦ ሲያደርጉ የቆዩና በታሪክም የመጀመሪያዋ ሴት የካውንስሊንግ ሳይኮሎጂ ባለሙያም ናቸው። የ2ኛ ዲግሪ ትምህርታቸውን በውጭ ሀገር ፊሊጲንስ የተማሩ ሲሆን ወደ ሀገራቸው በመመለስ ለረጅም ዓመታት በኮተቤ መምህራን ኮሌጅ (በአሁኑ ወቅት ኮተቤ ሜትሮፖሊቲያን ዩኒቨርሲቲ) እንዲሁም በአዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ አስተምረዋል። በኮተቤ መምህራን ኮሌጅም የጋይዳንስና ካውንስሊንግ ማዕከልን በማቋቋም ለተማሪዎችና ለኮሌጁ ማህበረሰብ አገልግሎቱን መስጠት ችለዋል። ከወ/ሮ ሰሚራ አልሀዲ በፊት ብዛት ያላቸውን የሳይኮሎጂ ተማሪዎችን በማስተማር ወ/ሮ አልማዝ እሸቴ ትልቅ ሚና የነበራቸው ሲሆን በሀገራችን የመጀመሪያዋ ኢትዮጵያዊት ሴት የከፍተኛ ትምህርት መምህርትና በሙያቸውም ሳይኮሎጂስት እንደነበሩ ለማወቅ ተችሏል። ወ/ሮ አልማዝ እሸቴ በቀጥታ ከካውንስሊንግ ሳይኮሎጂ ስልጠና ጋር ግንኙነት ባይኖራቸውም ለካውንስሊንግ ሙያ ደጋፊ የሚሆኑ ኮርሶችን በማስተማር ዲፓርትመንቱን

በማጠናከርና የተለያዩ ስልጠናዎችን በማዘጋጀት ረገድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክተዋል፡፡

በተለያዩ ወቅቶች በዩኒቨርሲቲው በተፈጠሩ አስተዳደራዊና ተቋማዊ አደረጃጀቶች ምክኒያት የሳይኮሎጂ ት/ክፍል የኢዱኬሽናል ሳይኮሎጂ ዲፓርትመንት (1966-1995 ዓ.ም)፣ ሳይኮሎጂ ዲፓርትመንት (1995 – 2003 ዓ.ም) ፣ የሳይኮሎጂ ኢንስቲትዩት (2004 – 2005 ዓ.ም) እና አሁን የሚጠራበትን የሳይኮሎጂ ትምህርት ቤት (ከ2006 ዓ.ም ጀምሮ) ስያሜዎችን ያገኘ ሲሆን በተጨማሪም በተለያየ ጊዜ በሶሻል ሳይንስ ኮሌጅ እና በትምህርት ፋክልቲ ስር እየተቀያየረ ሲመራ ቆይቷል፡፡ በዚህም ሳቢያ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በካውንስሊንግ ሳይኮሎጂ ሞያና አገልግሎት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ፈጥሯል፡፡ በተለይም በ1977 ዓ.ም በሶሻል ሳይንስ ኮሌጅ ስር ገብቶ የነበረ ሲሆን በወቅቱም የካውንስሊንግ ትምህርት ትኩረት እንዲነፈግ አድርጎታል፡፡ ቀጥሎም የሳይኮሎጂ ፕሮግራም በድጋሚ በ1984 ዓ.ም ወደ ትምህርት ፋክልቲ ከተመለሰ ቡኃላ የካውንስሊንግ ትምህርት ዳግም ትኩረት በማግኘት አንሰራርቷል፡፡

## ዘመናዊ የካውንስሊንግ ሳይኮሎጂ አገልግሎት

በዘመናዊ እና ሙያዊ መልክ የካውንስሊንግ አገልግሎት በቀጥታ ከኢትዮጵያ ህዝብ ጋር የተዋወቀው በ1980 ዎቹ መጀመሪያ ሲሆን፤ የኤች አይ ቪ ኤድስ የካውንስሊንግ አገልግሎትን እንቅስቃሴ መሰረት አድርጎ ነበር፡፡ ቀዳሚ የሆነውና በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ብሄራዊ የኤች አይ ቪ ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ሴክሬተሪያት ጽ/ቤት ድጋፍ የተዘጋጀው የኤች አይ ቪ ኤድስ ካውንስሊንግ ስልጠና ማንዋል መሰረታዊ የሆነ የካውንስሊንግ ዕውቀትና ክህሎት የተካተቱበት በመሆኑ በመላው ሀገሪቱ የሚገኙ የኤች አይ ቪ ኤድስ ካውንስለሮችን (HIV Counselors) ለማሰልጠን የካውንስሊንግ ሳይኮሎጂ ባለሙያዎች ድጋፍ አስፈላጊነት በመንግስት እየታመነበት በመምጣቱ ለሙያው በአንፃራዊነት ትኩረት እየተሰጠው መጣ (MOH, 1995)፡፡ በተያያዘም የወገን ኤድስ ቶክ ላይን 952 ቀጥታ የስልክ ካውንስሊንግ አገልግሎት በ2004 ዓ.ም ስራ በመጀመሩ ሙያውን በማስተዋወቅ የበኩሉን ድርሻ እየተወጣ ይገኛል፡፡

የካውንስሊንግ አገልግሎት ለመስጠት በአሁኑ ወቅት የተለያዩ የግል ድርጅቶች ከሚመለከታቸው የመንግስት አስፈጻሚ አካላት የሙያና ንግድ ፍቃድ በመውሰድ አገልግሎቱን ለማህበረሰቡ ተደራሽ ለማድረግ ጥረት እያደረጉ የሚገኙ ሲሆን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የካውንስሊንግ ሳይኮሎጂ አገልግሎትን የሥነ-ማህበረስብ በለሞያዎች፣ ሶሻል ወርከሮች፣ እንዲሁም ሌሎች ተያያዥ የእገዛ ሙያተኞች (helping professionals) በሰፊው መስጠት ጀምረዋል፤ አልፎ አልፎም በየትኛውም መልኩ ከሙያው ጋር ቅርበት በሌላቸው ግለሰቦች እየተሰጠ ይገኛል፡፡ በዚህም ምክኒያት በሙያው አገልግሎት፣ ጥራትና ውጤታማነት ላይ የተለያዩ ሞያዊና ስነ ምግባራዊ ጥሰቶች ይስተዋላሉ ሆኖም ግን አገልግሎቱን ብቃት ባላቸው የሳይኮሎጂ ባለሙያዎች ለመስጠት በርከት ያሉ ችግሮች ይታያሉ፡፡ ለምሳሌ የአገልግሎት ዘርፉ መሰረታዊ ችግር ከመንግስት የሚገባውን ያህል ትኩረት ማጣቱ ቢሆንም በመርህ ደረጃ የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃ ግብር አራትና አምስት (Education Sector Development Program IV and V (ESDP IV (2003 - 2007 ዓ.ም) and (ESDP V (2008 - 2012 ዓ.ም) በየትምህርት ቤቱ የጋይዳንስና ካውንስሊንግ ባለሙያዎች እንዲኖሩ አቅጣጫ ያስቀመጠ እንዲሁም የሀገሪቱ የጤና ፖሊሲ በተለይም

ብሔራዊ የአእምሮ ጤና ስትራቴጂ (National Mental Health Strategy of Ethiopia (2005 ዓ.ም) በአገሪቱ ካለው የአእምሮና የስነ ልቦና ጤና ችግር ተጠቂ ህሙማን ቁጥር መጨመር አንፃር ተመጣጣኝ የሆነ የሥነ አእምሮ ሀኪሞችና ነርሶች፣ ክሊኒካልና ካውንስሊንግ ሳይኮሎጂ ባለሙያዎች እንዲኖሩና የከፍተኛ ትምህርት ስልጠና ስርዓቱም ይህን ከግምት ውስጥ ያስገባ እንዲሆን በግልፅ በስትራቴጂው የሚያስቀምጥ ቢሆንም ዘርፉን በጠቅላላው የሚመራ፣ የሚያስተባብር ፣ የሚያስፈጽም እንዲሁም የሙያ ደረጃና ፍቃድ የሚሰጥ ራሱን የቻለ የአስፈፃሚ አካል በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱና በክልል ጤና ቢሮዎች በተደራጀ መልኩ ባለመኖሩ በአእምሮ ጤና ስትራቴጂ የተቀመጡ ግቦችን ለማሳካት ከፍተኛ እጥረትና ድክመቶች ጎልተው እንዲታዩ አድርጎል።

በሌላ በኩል በ2007 ዓ.ም የመጀመሪያው የሆነው የ8016 የቀጥታ ስልክ የካውንስሊንግ ሳይኮሎጂ አገልግሎት ተጀምሮ ህብረተሰቡ ለሙያው የተሻለ ግንዛቤ እንዲኖረው አድርጎል። በሚዲያው ዘርፍም በተለይ በ ኤፍ ኤም 97.1 የስነ ልቦና ፕሮግራም ፣ በሬዲዮ ፋና ኤፍ ኤም 98.1 የሚተላለፈው የእርቅ ማዕድ የሬድዮ ዝግጅት ካውንስሊንግ ሳይኮሎጂ በማህበረሰቡ ውስጥ የሚፈጠሩ ማህበራዊና ስነ ልቦናዊ ችግሮች ሞያዊ በሆነ መልኩ ሊፈቱ እንደሚችሉ እና የሚፈቱ መሆኑን በማስተዋወቅ ቀዳሚ ፕሮግራሞች ተደርገው ይወሰዳሉ።

በአዲስ አበባ ዩንቨርሲቲና በጥቂት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የካውንስሊንግ ሳይኮሎጂ ትምህርት በ 2ኛ ዲግሪ ደረጃ እየተሰጠ የሚገኝ ሲሆን። እንደ ባህር ዳር እና ወልዲያ ዩኒቨርስቲ ያሉት ደግሞ በስኩል ሳይኮሎጂ ዘርፍ በመጀመሪያ ዲግሪ በማሰልጠን ላይ በመሆናቸው በመጀመሪያ ደረጃና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እንዲሁም በከፍተኛ ትምህረት ተቋማት የጋይዳንስና ካውንስሊንግ አገልግሎት ወደፊት ይጠናከራል ተብሎ ይገመታል።

## በቀጣይ ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገቡ ተግባራት

የካውንስሊንግ ሳይኮሎጂ ሙያ እንዳሳለፈው የሀያ እና ሰላሳ ዓመት ዕድሜ በየደረጃው እያደገ የመጣ ቢሆንም ብቃት ያላቸው ባለሙያዎችን በማፍራት ረገድ ዩኒቨርሲቲዎች የጎላ ክፍተት ይታይባቸዋል። በዋናነት በሳይኮሎጂ የመጀመሪያ ዲግሪ አገልግሎቱን በብቃት መስጠት የማይቻል ሲሆን የካውንስሊንግ ሳይኮሎጂ ሙያን በድህረ ምረቃ ትምህርት ደረጃ ባሉት ዩኒቨርሲቲዎች በማስፋፋትና ስልጠናውን በጥራት በመስጠት በርካታ ማህበራዊና ስነ ልቦናዊ ክፍተቶችን መሙላት ይቻላል። ለዚህም መሳካት የ2ኛ ዲግሪ የካውንስሊንግ ሳይኮሎጂ ስልጠናን መግቢያ መስፈርቶችን ጠንካራ በማድረግ፤ የሰልጣኞች ምልመላና መረጣ ላይ ከፍተኛ ጥንቃቄ በማድረግ፣ ስልጠናውን ተግባር ተኮር በማድረግ እና በኢትዮጵያ ካውንስሊንግ ሳይኮሎጂ ባለሙያዎች ማህበር የሚዘጋጁ የሙያ ፍቃድ ማግኛ መስፈርቶችን አለማቀፋዊ ደረጃቸውን የጠበቁ እንዲሆኑ በማስቻል በቃት ያላቸው ምሩቃንን ማፍራት ይቻላል።

በተጨማሪም የመንግስት፣ መንግስታዊ ያልሆኑ እና የግል ተቋማት በስራቸው ተቀጥረው አገልግሎቱን ለሚሰጡ የካውንስሊንግ ሳይኮሎጂ ባለሙያዎች ተከታታይ እና ከወቅቱ ጋር የሚያራምድ የስራ ላይ ስልጠና በመስጠት አቅማቸውን በማሳደግ ስነ ልቦናው ጠንካራ የሆነ ጤናማ ማህበረሰብ መገንባት ያስችላል። በስልጠናው ዙሪያ ጥያቄው ንድፈ ሀሳብ ቀድሞ ለተማሪዎች መስጠት አልያም

ተግባር መቅደም አለበት ሳይሆን ሁለቱም ተያይዘው ቢቀርቡ የላቀ ዕውቀት እና ተግባራዊ ክህሎት ናብቃት ያላብሳቸዋል፡፡

በተለያዩ አካላት ለሚፈጸም የካውንስሊንግ አገልግሎት ሙያዊና ስነ ምግባራዊ ጥሰት ጠያቂ ይኖር ዘንድ የኢትዮጵያ ሳይኮሎጂ ባለሙያዎች ማህበር የበኩሉን ድርሻ መጫወት ይኖርበታል፡፡ በቀጣይም የኢትዮጵያ ካውንስሊንግ ሳይኮሎጂ ባለሙያዎች ማህበር በመመስረት የካውንስሊንግ አገልግሎት ፍቃድ መስጠት ላይ፣ ለባለ ሙያዎች ወቅቱን የጠበቀ ተከታታይ ስልጠናዎችን በማዘጋጀት፣ የባለሙያዎችን መብት ማስጠበቅ፣ ማህበራዊ ሀላፊነታቸውን በአግባቡ እንዲወጡ በማበረታታት እንዲሁም በሚፈጠሩ ሙያዊ ጥሰቶች ግለሰቦችንና ተቋማትን የሚደረግበትን ስርዓት በመዘርጋት ለዘርፉ ዕድገት የበኩላቸውን አስተዋፅኦ ሊያደርጉ ይገባል፡፡

በዘመናዊ ዓለም በተለያዩ ሙያዎች የሚፈፀሙ የቅንጅት ስራዎች ተመራጭ በመሆናቸው የካውንስሊንግ ሳይኮሎጂ፣ የክሊኒካል ሳይኮሎጂ፣ የስነ ማህበረሰብ፣ የልዩ ፍላጎት ትምህርት፣ የስነ አእምሮ ሀኪሞችና ነርሶች፣ የሶሻል ወርክ ባለሙያዎች፣ የስነ መለኮት ባለሙያዎች፣ የንግግር ህክምና ባለሙያዎች፣ ወዘተ በተጠና እና በተመረጡ ጉዳዮች ላይ በጋራ ቢሰሩ መልካም ሲሆን ያም ሆኖ የሚሰሩት ስራ ላይ ግልጽ የሆነ ሙያዊ እና ስነ ምግባራዊ ገደቦችንም ማበጀት ግድ ይላል፡፡

## ዋቢ ምንጮች


Abebech Asfaw, (1981). The Situation of Guidance & Counseling Services in Government Senior Secondary Schools in A.A.

Addis Ababa University Senate Legislation (2013).

Ministry of Education (1994). Education and Training Policy (1st ed.). Addis Ababa: St. George Printing Press

Ministry of Education (2015). Education Sector Development Program V (ESDP V) (2015/16 - 2019/20). Addis Ababa.

Ministry of Health – DPCD (1995). National HIV/AIDS Counseling Training Manual. A.A.

Ministry of Health (2012/13) . National Mental Health Strategy (2012/13-2015/16).

Yusuf O. Abdi & Amare, Bulti. Assessment of practices, problems of counseling services in some selected secondary school of A.A.

Yusuf O. Abdi, (1991). The secret of academic success. Addis Ababa, Ethiopia.

Yusuf O. Abdi, Zelalem Fekadu and Kebede, (1982). Guidance and Counseling In Institutions of Higher Learnings in Ethiopia-Future Perspective.

Yusuf Omer Abdi, (1967). The role of guidance and counseling in Ethiopian schools, MA thesis, University of Utah, USA.

Yusuf Omer Abdi, (1975). The problems and prospects of psychology in Africa. International Journal of psychology. Vol. 10, No 3, 227-234.